የተለያየ ዓይነት ቋንቋ ቢናገሩም ወይም ምን ያህል ጊዜ አውስትራሊያ ውስጥ ቢኖሩም ነገር ግን **ሁሉም ሴቶች የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ በየ 5 ዓመታት ማካሄዱ** አስፈላጊ ነው።

## በራስ ናሙና መሰብሰብ ምንድ ነው?

**ለማህጸን ማጣሪያ ምርመራ (Cervical Screening Test) ናሙና በራስ-መሰብሰብ ይህም አንድ ሴት በጥጥ መጥረጊያ በመጠቀም የራስዋን ናሙና ስትወስድ ነው። ይህ ምርመራ የሚካሄደው በግላዊ የሀኪም ወይም በሌላ የጤና ጥበቃ የተቀናጀ እና ብዙጊዜ የሚካሄደው መጋረጃ መከለያ ባለበት ወይም በመታጠቢያ ክፍል ውስጥ ነው።**

በራስዎ-መሰብሰብ ሊፈቀድልዎ የሚችለው እርስዎ:

- እድሜዎ 30 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ እና
- በሁለት ዓመታት የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ ጊዜ ካለፈ እንዲሁም
- ከጤና ሙያተኛ የቀረበልዎን የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ እምቢ ካሉ ነው።

ለማህጸን ማጣሪያ ምርመራ በራስዎ-መሰብሰብ ሁሉም ሴቶች ስለማይፈቀድላቸው ታዲያ መጀመሪያ ለሀኪምዎት ማነጋገሩ አስፈላጊ ነው።

### ለበለጠ መረጃ

ለነቀርሳ መረጃና ድጋፍ አቅራቢ በስልክ **13 11 20** መደወል።
በራስዎ ቋንቋ የሆነ ሰው ለማነጋገር ከፈለጉ፤ እባክዎ በስልክ **13 14 50** ይደውሉና ከ Cancer Council Victoria ጋር እንዲያነጋግርዎ መጠየቅ።
ለማህጸን ማጣሪያ ምርመራ ቀጠሮ ለማቀናጀት ከርስዎ ሀኪም ወይም ነርስ ጋር መነጋገር። በድረገጽ ላይ ገብቶ ማየት **www.cancer.org.au/cervicalscreening**

ታህሳስ 2018
የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ ማካሄድ ለሁሉም ሴቶች አስፈላጊ ነው።. AMHARIC

# የማህጸን ማጣሪያ ማካሄድ ለሁሉም ሴቶች ጠቃሚ ነው።



Cancer Council

# የማህጸን ነቀርሳ እና የሴት ብልት ቫይረስ ብክለት/ human papillomavirus (HPV)

የማህጸን ነቀርሳ ማለት የታችኛው ማህጸን ክፍል ነቀርሳ ነው። የርስዎ ታችኛው የማህጸን ክፍል በእምስዎ ውስጥ እንደሆነና የሚገኘውም በርስዎ ማህጸን መክፈቻ ላይ ነው።

በአጠቃላይ ሁሉም የማህጸን ነቀርሳዎች የሚከሰቱት በሴት ብልት ቫይረስ **(HPV)** መበከል ነው። **HPV** የቆመው ለሴት ብልት ቫይረስ ሲሆን በጣም የተለመደ ተላላፊ በሽታ እንደሆነና ብዙጊዜ የሚታይ በሽታ ምልክት የለውም። ቫይረሱ በወሲባዊ ግንኙነት እንደሚተላለፍ እና ሁለቱንም ማለት ወንዶችንና ሴቶችን ሊበክል ይችላል።

አብዛኛውን የተላላፊ ቫይረስ **(HPV)** ብክለት በተፈጥሮ ሰውነት ማጥፋት ሲችል ነገር ግን ካልቻለ አንዳንድ የቫይረስ **(HPV)** ዓይነቶች በርስዎ የታችኛው ማህጸን ክፍል ባሉት ሴሎች/ህዋሳት ላይ ለውጥ ያስከስታል። የእነዚህ ህዋሳት ሴሎች ለውጥ ቀደም ብሎ ካልታወቀና ህክምና ካላገኘ ወደ ነቀርሳ ሊቀየር ይችላል።

## እንዴት የ HPV ይታወቃል?

የ HPV ቫይረስን ለማየት በጣም ጥሩ የሆነው ዘዴ የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ ነው። በሀኪም ወይም ነርስ በኩል የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ መቅረብ ይችላል።

## የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ ማካሄድ ይኖርብኛልን?

እድሜዎ ከ25 እስከ 74 ዓመት ለሆኑ ሴቶች እና ወሲባዊ ግንኙነት አካሂደው ከሆነ የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ በየአምስት ዓመት እንዲያካሂዱ ይመረጣል።

**አሁንም የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ አስፈላጊ የሚሆነው እርስዎ:**

- የHPV ክትባት ወስደው ከሆነ
- የወር አበባ መቆም/ማረጥ ጊዜዎን ካሳለፉ
- አንድ ብቻ የወሲባዊ አጋር ከነበረዎት
- በባህላዊ ግርዛት ካካሄዱ
- ልጅ ካለዎት
- አግብተው ከሆነ
- ተፋተው ከሆነ
- ባሏ የሞተባት ከሆኑ ነው።

መከላከል ከሚቻሉት አብዛኞች ነቀርሳዎች ውስጥ የማህጸን ነቀርሳ አንዱ ይሆናል።

## የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ እና የሴት ብልት ግርዛት (FGC)

የሴት ብልት ግርዛት (FGC) በማካሄድ አንዳንዴ ሴቶች የማህጸን ማጣሪያ ምርመራ ላለማድረግ ሊያግዳቸው ይችላል። ይህንን ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት የሚችሉት:

- የሚቀናጀው ቀጠሮ ግላዊና ሚስጢራዊ ስለመሆኑ ለማወቅ
- በበለጠ ምቾት እንዲሰማዎ እንዲረዳዎ ዘመድ ወይም ጓደኛ ከርስዎ ጋር ለመውሰድ
- የሴት ነርስ ወይም ሀኪም ለመጠየቅ
- ይህ ከመፈጠሩ በፊት ስላለ ምርመራ ለርስዎ ነርስ ወይም ሀኪም ለመጠየቅ
- በማንኛውም ጊዜ ምርመራዊ ለማቆም ወይም ለማዘግየት
- በምርመራ ጊዜ ለርስዎ የማስቀመጫ ወረቀት ለመጠየቅ ነው።